# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ኢየሱስ እና ዘኪዮስ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



አንድ ቀን ፣ ኢየሱስ
በኢያሪኮ ያልፍ ነበረ፡፡
ይህቺ ከተማ ከብዙ
አመታት በፊት በኢያሱ
ፈርሳ ነበረ፡፡ አሁን
ዳግም ተገንብታ
ብዙዎች በዚያ እየኖሩ
ነው፡፡ ከእነርሱም
መካከል ዘኪዮስ
የሚባል ሰው ነበረ፡፡



በኢያሪኮ ይኖሩ የነበሩ ሌሎች ሰዎች ፣ ቀረጥን
ከእነርሱ ይሰበስብ ስለነበረ ፣ ዘኪዮስን አይወዱትም
ነበረ፡፡ ዘኪዮስ የተወሰነ ያክሉን ገንዘብ ለመንግስት
ልኮ የተቀረውን ለራሱ አስቀርቷል፡፡

ቀረጥ ሰብሳቢ መሆኑ ዘኪዮስን እጅግ ባለጠጋ አድርጎታል፡፡ ቤቱ ካሉት ቤቶች ሁሉ ምንአልባት ትልቁና እጅግ ተመራጩ ሳይሆን አይቀርም፡፡



ነገር ግን እጅግ አጭር ነበረ፤
አጥረቱም በገንዘብ ሳይሆን
በቁመት ነበረ።





ዘኪዮስም ኢየሱስ በኢያሪኮ መሆኑን ሲሰማ ፣ ትንሹ ቀረጥ ሰብሳቢ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለውን ከናዝሬት የሆነውን ሰው ማየት ፈለገ። ነገር ግን ህዝቡ እጅግ ብዙ እና ረዣዥም ነበሩ።



ዘኪዮስ አንድ ሐሳብ ነበረው ፤
ከህዝቡ ፊት ሆኖ ዛፍ ላይ
መውጣትና ኢየሱስን ማየት
መቻል ነበረ፡፡

ዘኪዮስም በዋርካ ዛፍ በመውጣት
፣ ኢየሱስን እዚያ ሆኖ ለማየት
የሚመቸውን ቅርንጫፍ አገኘ፡፡
ምንአልባትም ፣ “ጥሩ የሆነ የማያ
ስፍራ አግንኝቼአለሁ” ሳይል
አይቀርም፡፡ “ሰዎች ሳያዩኝ እኔ
ማየት እችላለሁ፡፡”



“ዘኪዮስ ፣ ፍጠንና ውረድ!”፡፡
ትንሹ ቀረጥ ሰብሳቢ ጆሮውን
ማመን አልቻለም፡፡ ኢየሱስ ከዛፉ
ስር ቆሞ ነበረ፡፡ ኢየሱስ
ሲመለከተው ነበረ፡፡ ኢየሱስም
ይጠራው ነበረ፡፡





ኢየሱስ ሲጠራው ዘኪዮስ
ተደንቆ ከሆነ ፣ “ዛሬ በቤትህ
እሆናለሁ” ሲለው፣ ይበልጥ
ሳይደነቅ አይቀርም፡፡ ዘኪዮስ
ሊወድቅ በሚችልበት ልክ
እጅግ ፈጥኖ ከዛፉ ላይ ወረደ፡፡

ዘኪዮስም ኢየሱስ ቤቱን ሊጎበኝ እንደሆነ ስላወቀ እጅግ
በመደሰት ተነቃቃ፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ ይሄንን አልወደዱም
ነበረ፡፡ ኢየሱስ እንደ ዘኪዮስ አይነት ኀጢያተኛን
መጎብኘት የለበትም ብለው አስበው ነበረ፡፡





ኢየሱስ አዲስን ሕይወት
ለዘኪዮስ ይዞለት መጥቶ
ነበረ፡፡ ዘኪዮስም “ ጌታ
ሆይ ፣ እኔ እኩሌታዬን
ለድሆች እሰጣለሁ፡፡
ማንንም አታልዬ ቢሆን ፣
አራት እጥፍ መልሼ
እሰጣለሁ፡፡”

ኢየሱስም በዘኪዮስ አዲስ
ሕይወት ተደሰተ፡፡ እርሱ
ሰዎች ከኃጢያት ዘወር
ብለው ፣ ትክክል የሆነውን
ሲያደርጉ ይደሰታል፡፡
ኢየሱስም ፣ “የሰው ልጅ
የጠፋውን ሊፈልግና
ሊያድን መጥቷል፡፡”
በኢያሪኮም በዚያ ቀን
ኢየሱስ ዘኪዮስን አገኘው፡፡



# ኢየሱስ እና ዘኪዮስ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ 19

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

53

60

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16